Engda Kif:

Engda Kif:

ጊዜ ጊዜን እየወለደው ትናንት በዛሬ ዛሬ ደግሞ በነገ ሊተካ ተፈጥሮ ግድ ነውና እንሆ ዛሬ ላይ እንደ አማራ በርካታ ፈተናዎችን አልፈን ስለ መፃዒው እጣ ፈንታችን ለመወሰን ሰብሰብ ብለን ለመምከርም በቅተናል። እዚህ ላይ አንድ የሚሰማኝን እውነታ ጀባ ልበላችሁ። "ቁርጠኝነት" ቁርጠኝነት አላማን ይጠይቃል፤አላማ ከውስጥ የመነጨ ፍላጎትን ያንፀባርቃል፤ የውስጥ ፍላጎታችን በምንሰማውና በምናየው ነገር ላይ መወሰኑ አያወላዳም።"የማያውቁት ሀገር አይናፍቅምና "ነው ቅሉ።

የብዙዎቻችን ችግር በእኛነታችን እና በአላማችን መካከል ነው።ለዚህም ታሪክአልስ አለው።"ከታሪክ የተማርን እና የምንማር የአባቶቻችን ልጆች ነንና"

" ታሪክ ለኛ ምን በጀ? ምንስ ይጠቅመናል?"ብለውም የሚጠይቁ አይታጡምና ዋናውን ታሪክ ለባለ ሙያው ትቼ እኔ ግን እላለሁ...

አይደለም የሰው ልጅ ቀርቶ ግዑዙን ህንፃ ለማነፅ ውስጣዊ መሬቱ ይጠናል፤ ድንጋዩ፣አፈሩ፣ አለቱ ምንነቱ ማንነቱ ይጠየቃል።ለዚህም ታሪክህ አንተ ነህ፤ ሰው ብቻ ሙሉ ይሆን ዘንድ ስጋ መልበስ ብቻ በቂ አይደለም። ታሪክህን ስታውቅ አንተነትክን ታውቃለህ ፤ካለፈው ማንነትህ በመረዳት ነገህንም ታንፃለህ፤ ካለፈው ህይወትህ አንተነትህን ታገኛለህ ። እውነቴን ነው! የአንድ መኪና ስፖኬ ርቀቱን ከቀደመውና ከመጭው አመጣጥና ለመጉዝ እንደሚጠቅም ሁሉ ታሪክ መረዳትም ላለፈው ማንነትህ እና ለሚመጣው አንተነትህ ወሳኝ ምዕራፍህ ነው።ያም ስለሆነ ታሪክ የሌለው ህዝብ ስፖኬ እንደሌለው መኪና ይቆጠራል።

ይህን ያልተረዱ ባለጊዜዎች ወይ ታሪክ ሳያውቁ ወይ በታርካቸው አፍረው ባለ ታሪኩ ህዝብ ላይ ባንድም በሌላም በፖሊሲ ሳይቀር ህዝብን ጠላት አድርገው ዘርፈ ብዙ ግፍ ፈፅመው አልፈዋል። ይሄው በአሁኑ ወቅትም ሁሉም ቤቱን ዘግቶ ባለበት ጊዜ በአንተ የተከፈተ ቤት ማንም ገብቶ እንዲወጣ የምትፈቅድበት ህሊናዊም ሆነ ሞራላዊ ህግ የለምናሽምላሽ መስጠት ተገቢ ስለሆነ አብን ተወልዷል።(መከላከል) መከላከል ተፈጥሯዊ ነዉ፤ በመንግስት ፖሊሲ ስናየዉ እንኳን አደጋን መከላከል፣ ድርቅን መከላከል፣ ኮሮናን መከላከል... ለመከላከልም ሃይል ያስፈልጋልና ሃይላችን እውነት እና አንድነት ነው። ባንድነት ጉዞ ውስጥም ስሜት ብቻውን ስኬት፤ እውቀት ብቻውን አቅም አይደለምና ሁለቱን አጣጥመን በስሜት እና በዕውቀት ድምር ውጤት ስሌት አዎንታዊ ግብዓትን በመቀዳጀት ለቆምንለት ህዝብ መድረስ እና ወቅቱ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁነት ይፈልጋል።

ለዚህም እላለሁ በስንኝ ቋጠሮ

ጊዜ ቆሞ ላይቀር ሞት ላይሰጥ ቀጠሮ።

ያኔ ተብለህ ነበር

በያደባባዩ በቃ ሰብረነዋል፣

እንደ ሲጋራ ጢስ ረግጠን ጥለነዋል፣

አከርካሪዉ መተን ከንቱ አድርገንዋል።

ይኸው አሁን ላይም ፣ይህ ቃል ይፈፀም ዘንድ፤

ካንተ ወገን ብቻ፦

17 ልጆች ሴቶች ታግተዋል፣

45 ሽዎች ት/ርት አቋጠዋል።

ይህ ጥላቻ አይደለም ወይም መበሻሸቅ፣

ነገር ግን እውነታዉ ሲታይ ሳይደበቅ፣

ወቅቱ ይጠይቃል መመከት መጠንቀቅ።

ማስተዋልም ያሻል ፍትህ ጎራ አትለይም፣

የምትገኝበት ጊዜው ቢለያይም።

ብዙ መከራና ብዙ ጉድ አልፈናል፤

በየገበያዉ ላይ ህይወት ተነጥቀናል፣

በየ አደባባዩ ነብሶች ገብረናል፤

እኛ አንፈራም ብሎ አነምነም ቢላቸው

አሳምነዉ ብለዉ ጦር ልከውብናል፤

በአጣዬ መተከል በጎጃም በጎንደር ጀግና አሰውተናል።

ግን እንዲህም ሆኖ

እንዲህ ኖረን ኖረን ሆነን በደለኛ፤
ተገፍተን ተገፍተን ብንሆን ብሄርተኛ፤
ሌላውን አንገፋም ጤነኞች ነን እኛ።
አዎ ጤነኞች ነን!
ጤነኛ ገበሬ፤ጤነኛ አስተማሪ፤
ጤነኛ መሀንዲስ፣ ጤነኛ ገባሪ፤
ጤነኛ ባለሀብት፣ ጤነኛ ተማሪ፤
ጤነኛ ባለዉቀት፣ጥበብን ፈጣሪ፤ ጤነኛ አስተዋይ ህዝብ ጤነኛ ታታሪ፤
ጤነኛ አገር መስራች ድንበር አስከባሪ፤
አዎ ጤነኞች ነን!
ጤነኛ ብሄርተኛ!
ጤነኛ ጢነኛ!
ጤነኛ ነፍጠኛ!
የማንንበረከክ ለማንም ጎጠኛ።
ከዚህ ዉስጥ ተውጣጥተን፣
በበደል ተገፍተን፤
ዛሬ 1 ሆነናል፤
ጎንደር ሸዋ ጎጃም ወሎ ቃል ገብተናል፤
አማራነት እንጂ ጎጥ ማለት ትተናል
የለም በታሪክም የለም በባህላችን፣
ዛሬም 1 ሆነን እንዳባቶቻችን፣
አፈር ሲደፋብን በቅኔ እየወዛን፣
ባይወጉን አይደለም በቅኝ ያልተገዛን፣
ተቸግረው እንጂ ስንሞት እየበዛን፣
እንዳለው ጠቢቡ!
ታላላቆቻችን በከፈሉልን ደም፤
ባማራነት ስሪት ኢትዮጵያችን ትቅደም።
እንግዳሸት ነኝ!